ስለ የ2012 DC HealthCare Alliance ጥቅም የማግኘት ተገቢነት
የተደረጉ ለውጦች ብዙ ጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት መንግስት
የጤና እንክብካቤ ፋይናንስ ክፍል

ስለ የ2012 DC HealthCare Alliance ጥቅም የማግኘት ተገቢነት
የተደረጉ ለውጦች ብዙ ጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

በDC HealthCare Alliance ጥቅም የማግኘት ተገቢነት ያለው ማን ነው?

በDC HealthCare Alliance የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚከተሉትን ማሟላት ያስፈልጋል፤

- የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ነዋሪ መሆን አለብዎት፣
- ዕድሜዎ 21 ወይም ከዛ በላይ መሆን አለበት፣
- Medicaidን ጨምሮ ሌሎች የጤና ኢንሹራንሶች ተጠቃሚ መሆን የለብዎትም፣
- አጠቃላይ ገቢዎ ከ$1,861.67 (ለግለሰብ) እና ከ$2,521.67 (ለጥንዶች) መብለጥ የለበትም፣ እና
- ከ$4,000 (ለግለሰብ) እና ከ$6,000 (ለጥንዶች/ ለቤተሰቦች) የሚበልጥ ዋጋ ያለው ንብረት ሊኖሮዎት አይገባም፡፡

የDC HealthCare Alliance ጥቅምን ለማግኘት እንዴት አመለክታለሁ?

ለDC HealthCare Alliance ለማመልከት፣ የሚከተለውን ማድረግ አለብዎት፤

- የሕክምና ድጋፍ ለማግኘት የተዘጋጀውን የD.C Combined ማመልከቻ መሙላት፣
- ዲሲ ውስጥ እንደሚኖሩ ማስረጃ ማቅረብ፣
- የማናቸውም ገቢዎችዎ ወይም ንብረትዎችዎ ማስረጃ ማቅረብ፣
- የማህበራዊ ዋስትና ካርድ ካልዎት፣ በቃለ መጠይቁ ወቅት ማቅረብ ይኖርቦታል፣
- ግሪን ካርድ ካልዎት፣ የውጭ ዜጋ ነዋሪነት ፈቃድ ቁጥርዎን (ኤሊን ቁጥር) ወይም የማህበራዊ ዋስትና ካርድዎን ማቅረብ ይኖርቦታል፣
- ቀጣይነት ያለው ተገቢነት እንዲኖርዎት በየስድስት (6) ወሩ በማናቸውም ESA Service Centers (Section 3305.1 District of Columbia Register Vol. 58-No. 39 September 30, 2011) በመገኘት ፊት ለፊት የሚደረግ ቃለ መጠየቅ መደረግ አለብዎት፡፡

ለDC HealthCare Alliance የት ማመልከት እችላለሁ?

- ❑ Enrollment Broker's Office:
  6856 Eastern Avenue NW
  Washington, D.C 20012
  (202) 639-4030
  1-800-620-7802 and TTY/TDD at (202)-639-4041

ስለ የ2012 DC HealthCare Alliance ጥቅም የማግኘት ተገቢነት
የተደረጉ ለውጦች ብዙ ጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

- በ Department of Human Service፣ Economic Security Service Centers (የሰብዓዊ አገልግሎት ክፍል፣ የኢኮኖሚ ደህንነት አገልግሎት ማዕከላት)፤

  - Congress Heights - 4001 South Capital St., S. W.
  - Fort Davis - 3851 Alabama Ave., S.E.
  - Anacostia - 2100 MLK Jr Ave, S.E.
  - Taylor Street - 1207 Taylor Street, N.W
  - H Street - 645 H Street, N.E.

- በሚከተሉት የሕክምና ተቋማት፤

  - Southwest Health Clinic - 850 Delaware Ave., S.W
  - Upper Cardozo Clinic - 3020 14th St., N.W
  - La Clinical Clinic - 2831 15th St., N.W
  - Providence Hospital - 1150 Varnum St., N.E.
  - Children Hospital - 111 Michigan Ave., N.W
  - United Medical Center - 1310 Southern Ave., S.E.

በስልክ ወይም በደብዳቤ ማመልከት እችላለሁ?

በስልክ ማመልከት አይችሉም፡፡ ማመልከቻ በደብዳቤ መላክ ይችላሉ ሆኖም ግን በአካል በመቅረብ ቃለ መጠይቅ መደረግ ይኖርቦታል፡፡

በአካል በመቅረብ በሚደረገው ቃለ መጠየቅ ቀን ብታመም ወይም መምጣት ባልችልስ?

የምርመራ ውጤት እና የሕክምና መላምትን ያካተተ እንደታመሙ ወይም የአካል ጉዳት እንደደረሰቦት የሚገልጽ በዶክተር የተጻፈ ደብዳቤ ማስገባት ይችላሉ፡፡ የሐኪም ወረቀቱ የጤናዎ ሁኔታ ማመልከቻ ለ45 ቀናት ማመልከቻ ለማቅረብ ወይም ለ90 ቀናት ዳግም ማረጋገጫ ለማግኘት ወደ ቃለ መጠይቁ መምጣት እንደማይችሉ በተጨማሪ መግለጽ አለበት፡፡

ዕድሜዎ 65 እና ከዛ በላይ ከሆነ፣ እና ዕድሜዎ ከቤትዎ ለመውጣት የማያስችሎት ከሆነ፣ ይህንኑ በመግለጽ ለምን መምጣት እንደማይችሉ መግለጫ ጽሑፍ መጻፍ ይችላሉ፡፡

ወደ Alliance ፕሮግራም ከማለከትኩ በኋላ ተገቢነት እንዳለኝ ለማወቅ ምን ያክል ጊዜ ይወስዳል?

አንድ ጊዜ ESA አስፈላጊውን መረጃ ካገኘ እና በአካል ቀርበው ቃለ መጠይቅ ከተደረገልዎት በኋላ፣ ብዙውን ጊዜ እስከ ሁለት ሳምንት ጊዜ ይወስዳል፡፡

ያገኘሁት የተገቢነት መብት ምን ያክል ጊዜ ይቆያል?

የተገቢነት መብት ለስድስት (6) ወራት ይቆያል፡፡ ሆኖም ግን፣ በAlliance ፕሮግራም ለመቆየት፣ ዳግም ማረጋገጫ/ ዕድሳት ቅጹን መሙላት፣ በየስድስት ወሩ በአካል በመቅረብ ቃለ መጠየቅ መደረግ እና የነዋሪነት እና የገቢ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይኖርቦታል፡፡

ስለ የ2012 DC HealthCare Alliance ጥቅም የማግኘት ተገቢነት
የተደረጉ ለውጦች ብዙ ጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

ዳግም ማረጋገጫ ጊዜ እንደደረሰ በምን አውቃለሁ?

Department of Human Service's Economic Security Administration (ESA) (የሰብዓዊ አገልግሎት ክፍል የኢኮኖሚያዊ ደህንነት አስተዳደር) የዳግም ማረጋገጫ ወይም ዕድሳት ማሳሰቢያ ደብዳቤ ይልክሎታል፡፡

አመልካች/ ተቀባይ ወይም ሕጋዊ ወኪል እንዴት ይታለፍልኝ ብሎ መጠየቅ ይችላል?

ለአካል ጉዳት ያለባቸው ወይም የታመሙ ሰዎች፣ አመልካቹ/ ተቀባይ ወይም ሕጋዊ ወኪሉ የሚከተሉትን ማስገባት አለባቸው፤

- አመልካቹ እንደታመመ፣ አካሉ እንደጎደለ የሚያረጋግጥ ከሆስፒታል ወይም ከሕክምና ባለሙ ያ የተሰጠ ቀን የተጠቀሰበትና የተፈረመበት የራስጌ ማህተም ያለው ደብዳቤ፡፡
- ጥያቄው ለESA Medical Review Team (MRT) (የሕክምና ገምጋሚ ቡድን) መቅረብ ያለበት ሲሆን ጥያቄው ሁሉንም መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ፣ ይታለፍልኝ ጥያቄው በMRT ይጸድቃል፡፡
- ተቀባይነት ሲገኝ ወይም የይታለፍልኝ ጥያቄው ውድቅ ሲደረግ፣ ለተጠቃሚው ወይም ለሕጋዊ ወኪሉ ማስታወሻ ደብዳቤ ይላክለታል፡፡
- ዕድሜያቸው 65 ወይም ከዛ በላይ ለሆኑ ሰዎች፣ በዕድሜ አንጋፋው ሰው ለምን መምጣት እንደማይችሉ ደብዳቤ መጻፍ ይችላሉ፡፡

አዲስ የተሰጠው የስድስት (6) ወር ጥቅም የማግኘት መብት ቀደም ሲል የአስራ ሁለት (12) ወር ጥቅም የማግኘት መብት ተሰጥቶዋቸው ለነበሩ የAlliance ተጠቃሚዎች ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድራል?

- በወቅቱ የአስራ ሁለት (12) ወር ጥቅም መብት የማግኘት መብት ያላቸው ተጠቃሚዎች ቀጣይ ጥቅም የማግኘት መብትን ለማስጠበቅ በአካል ቀርበው ቃለ መጠይቅ እንዲደረግላቸው ሊጠየቁ ይችላሉ፣ ተገቢነት ያላቸው ሆነው ከተገኙ ቤተሰቡ ወይም ግለሰቡ የስድስት (6) ወር ጥቅም መብት የማግኘት ማረጋገጫ ይሰጣቸዋል፡፡
- ተቀባዮች አዳዲሶቹን መስፈርቶች እስኪያሟሉ ድረስ ቢያንስ የሰላሳ (30) ቀን ጊዜ ይሰጣቸዋል፡፡

ዜግነት ያልተሰጣቸው ከውጭ የመጡ ሰዎች ለAlliance የዕድሳት/ ዳግም ማረጋገጫ ቅጽ ወስደው እንዲሞሉ ይጠበቅባቸው ይሆን?

አዎ፣ ዜግነት ያልተሰጣቸው ከውጭ የመጡ ሰዎች ለDC HealthCare Alliance የዕድሳት/ ዳግም ማረጋገጫ ቅጽ ወስደው እንዲሞሉ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ድርጅቶች በአመልካች ፈንታ ማመልከቻ ወይም ዳግም ማረጋገጫ ቅጾችን እንዲያስገቡ ይፈቀድላቸው ይሆን?

አዎ፣ ጠበቆች እና ሌሎች ድርጅቶች አሁንም ድረስ ቢሆን በቅርብ ጊዜ የተሞሉ ማመልከቻዎችን፣ ዕድሳት ወይም የዳግም ማረጋገጫ ቅጾችን በአመልካቾች ፈንታ ማስገባት ይችላሉ፣ ሆኖም ግን በአካል በመቅረብ የሚደረገው ቃለ መጠይቅ በራሳቸው በአመልካቾቹ ብቻ መከናወን አለበት፡፡ ጠበቆች ስለ አዳዲሶቹ መስፈርቶች በማስተማር ላይ ቢያግዙ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

ስለ የ2012 DC HealthCare Alliance ጥቅም የማግኘት ተገቢነት
የተደረጉ ለውጦች ብዙ ጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

ተጠቃሚዎች አድራሻቸውን እንደለወጡ ማሳወቅ ከፈለጉ፣ ወደ ESA ራሳቸው በአካል መሄድ አለባቸው ወይስ አሁንም ድርጅቶች አዲሱን መረጃ በፋክስ ወደ Change Center (ለውጥ ማሳወቂያ ማዕከል) መላክ ይችላሉ?

አድራሻቸው እንደለወጡ ማሳወቅ የሚፈልጉ አመልካቾች ወደ የESA አገልግሎት ማዕከላት መሄድ አይጠበቅባቸውም፡፡ የአመልካቾች አድራሻ ለውጥ መረጃ ወደ ESA Change Center (ለውጥ ማሳወቂያ ማዕከል) በፋክስ ቁጥር (202)-535-1664 መላክ ወይም በስልክ ቁጥር (202)-727-6600 ሊነገር ይችላል፡፡ ሆኖም ግን፣ ESA ግለሰቡን እና ወይም ቤተሰቡን አሁንም ቢሆን ተጨማሪ የሰነድ ማስረጃዎችን ወይም ማረጋገጫ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

ለDC HealthCare Alliance ተገቢነት ስለመኖሩ የተመለከቱ ጥያቄዎች፣ ካሉ እባክዎ የሚከተሉትን ያነጋግሩ፤

Lucy T. Wilson-Kear at (202)-442-8997 or email at lucy.wilson-kear@dc.gov
Danielle Lewis at (202)-442-8997 or email at Danielle.lewis@dc.gov
Anthony Proctor at (202)-442-9114 or email at Anthony.proctor@dc.gov
Richard Walker at (202) - 698-3958 or email at Richard.walker@dc.gov